## ውድ አንባቢ፤

ዘቡር (መዝሙረ ዳዊት) በብሉይ ኪዳን የተካተተ መጽሐፍ ነው። የዳዊት መዝሙር (22) ከክርስቶስ ልደት አንድ ሺ ዓመት በፊት በነቢዩ ዳዊት ተጻፈ።

አትኩሮታችን በመዝሙረ ዳዊት 22 ላይ ብናደርግ የነቢዩ ዳዊት አጻጻፍ፥ የከፋ ሥቃይ በተጋተ አሳዛኝ የሰቆቃ ዋይታ እናገኛለን። ምዕራፉን እያነበብን ስንዘልቅ ከአንድ ሺ ዓመታት በኋላ በተጻፈው ኢንጅል (ወንጌል) ውስጥ የሰፈሩ ጥቅሶች ያጋጥሙናል።

ይሁንና በመዝሙረ ዳዊት 22 ውስጥ ያሉትና በኢንጅል ውስጥ ያሉትን ጎን ለጎን እያመሳከርን ስናነብ፥ ነቢዩ ዳዊት የጻፈው የራሱን ሥቃይ በማውሳት ወይስ የሌላን ሥቃይ አስመልክቶ ነው የሚለውን ለመረዳት ያስችለናል። የዚሁ ሰው ሰቆቃም ከእግዚአብሔር የወረደን በረከት ለአንተና ለመላ የሰው ልጅ ይደርስ ዘንድ እንዴት ምክንያት እንደሆነ ትረዳለህ።

«የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹ የተወሰዱት ከአሮጌው ትርጉም ነው።»

«የቁርአን ጥቅሶች የተወሰዱት በ38 ኛው ዘመን ከታተመው የቁርአን መጽሐፍ ነው።»

## 1. በእግዚአብሔር የተረሳ የስቃይ ሰው ማን ነበር?

### ነቢዩ ዳዊት ምን ይሆን የጻፈው?

«አምላኪ፥ አምላኪ፥ ለምን ተውኸኝ? እኔን ከማዳንና ከጩኸቴ ቃል ሩቅ ነህ። አምላኪ፥ በቀን ወደ አንተ እጠራለሁ፥ አልመለስህልኝም፤ በሌሊትም እንኳ ዕረፍት የለኝም» መዝሙረ ዳዊት [22]፡ 1-2)።

### በኢንጅልስ የተጻፈው ምን ይላል?

በሰቀሉትም ጊዜ ሦስት ሰዓት ነበረ። ስድስት ሰዓትም በሆነ ጊዜ፥ እስከ ዘጠኝ ሰዓትም በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ። በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፡- ኤሎሄ፥ ኤሎሄ፥ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ትርጓሜውም አምላኪ፥ አምላኪ፥ ለምን ተውኸኝ ማለት ነው (ማርቆስ 15፡25፥33፥34)።

## 2. ለሰዎች ልግጫና ለውርደት የተዳረገው የሰቆቃ ሰው ማን ነበር?

### ነቢዩ ዳዊት ምን ሲል ጻፈ?

«እኔ ግን ትል ነኝ ሰውም አይደለሁም፤ የሰው ማላገጫ በሕዝብም ዘንድ የተናቅሁ ነኝ። የሚያዩኝ ሁሉ ይላገጡብኛል፤ ራሳቸውን እየነቀነቁ በከንፈሮቻቸው እንዲህ ይላሉ፡- በእግዚአብሔር ተማመነ፥ እርሱንም ያድነው፤ ቢወድደውስ ያድነው» (መዝሙረ ዳዊት [22]፡ 6-8)።

### በኢንጅል ምን እናነባለን?

«የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበርና፡- ቤተ መቅደስን የምታፈርስ በሦስት ቀንም የምትሠራው፥ ራስህን አድን፤ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ አሉት። እንዲሁም ደግሞ የካህናት አለቆች ከጻፎችና ከሽማግሎች ጋር እየዘበቱበት እንዲህ አሉ፡- ሌሎችን አዳነ፥ ራሱን ሊያድን አይችልም፤ የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ፥ አሁን ከመስቀል ይውረድ እኛም እናምንበታለን። በእግዚአብሔር ታምኖአል፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ

ብሎአልና ከወደደውስ አሁን ያድነው» (ማቴዎስ 27፡39-43)።

3. ሰዎች ሲገላምጡትና ሲጠቋቆሙበት የነበረው፥ የሰቆቃ ሰው ማን ነበር?

ነቢዩ ዳዊት ስለዚሁ ምን ሲል ጻፈ?

«አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ፤ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም» (መዝሙረ ዳዊት [22]፡ 17)።

ከኢንጅልስ ምን እናገኛለን?

«ሕዝቡም ቆመው ይመለከቱ ነበር። መኳንንቱም ደግሞ፡- ሌሎችን አዳነ፤ እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠው ክርስቶስ ከሆነ፥ ራሱን ያድን እያሉ ያፌዙበት ነበር» (ሉቃስ 23፡35)።

4. ልብሶቼን ሁሉ ዕጣ ተጣጥለው የተካፈሉበት ጎስቋላ ሰው ማን ነበር?

ነቢዩ ዳዊት ስለዚህ ምን ብሎ ጽፏል?

«ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ» (መዝሙረ ዳዊት [22]፡ 18)።

በኢንጅል የተጻፈውስ ምን ይላል?

«ጭፍሮችም ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶቼን ወስደው ለእያንዳንዱ ጭፍራ አንድ ክፍል ሆኖ በአራት ከፋፈሉት፤ እጀ ጠባቡን ደግሞ ወሰዱ። እጀ ጠባቡም ከላይ ጀምሮ ወጥ ሆኖ የተሠራ ነበረ እንጂ የተሰፋ አልነበረም። ስለዚህ እርስ በርሳቸው፡- ለማን እንዲሆን በእርሱ ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ አንቅደደው ተባባሉ። ይህም፡- ልብሴን እርስ በእርሳቸው ተከፋፈሉ በእጀ ጠባቤም ዕጣ ተጣጣሉበት የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው» (ዮሐንስ 19፡23-24)።



5. በጥማት የተሠቃየው ሰው ማን ነበር?

በዚሁ ላይ ነቢዩ ዳዊት ምን ሲል ጻፈ?

«ኃይሌ እንደ ገል ደረቀ፥ በጉሮሮዬም ምላሴ ተጣጋ፥ ወደ ሞትም አሸዋ አወረድኸኝ» (መዝሙረ ዳዊት [22]፡ 15)።

በኢንጅልስ ምን ይላል?

«ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደ ተፈጸመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ፡- ተጠማሁ አለ። በዚያም ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፤ እነርሱም ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው በሁሶፕም አድርገው ወደ አፉ አቀረቡለት። ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፡- ተፈጸመ አለ፥ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ» (ዮሐንስ 19፡28-30)።

6. እጆቼንና እግሮቼን በመቸንከር የተሰቃየው ሰው ማን ነበር?

ነቢዩ ዳዊት ይህን አስመልክቶ ምን ሲል ጻፈ?

«ብዙ ውሾች ከብበውኛልና፤ የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ፤ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ» (መዝሙረ ዳዊት [22]፡ 16)።

በኢንጅልስ ምን ተጽፎ ይሆን?

ሐዋርያው ዮሐንስ ከኢየሱስ ትንሣኤ በኋላ እንዲህ ጽፏል፡-

«ነገር ግን ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከእነርሱ ጋር አልነበረም። ሌሎቹም ደቀ መዛሙርት፡- ጌታን አይተነዋል አሉት። እርሱ ግን፡- የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው።

ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ፥ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ፡-

ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ከዚያም በኋላ ቶማስን፡- ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው። ቶማስም፡- ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፡- ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው» (ዮሐንስ 20፡24-29)።

በኢንጅሉ መሠረት፣ ኢየሱስ ሞትን አሸንፎ ከመቃብር እንደተነሣ ለምእመናን እንዲህ ሲል ተናገረ፡-

«ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፡- ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፣ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል» (ሉቃስ 24፡44-47)።



ውድ አንባቢ፣ ኢንጅልም እንዲህ ሲል ያረጋግጥልሃል፡-

«ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤» (1ኛ ጢሞ.1፡15)።

«ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው። አንድ እግዚአብሔር አለና፣ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፣ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ» (1ኛ ጢሞ.2፡4-6)።

«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።

«ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ።» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18)።

«በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፣ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፣ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» (ፊልጵ.2፡9-11)።

ልብ በል፡- መሢሑ ኢየሱስን እንደ አዳኝህና ጌታህ አድርገህ ትቀበለውና ታከብረው ዘንድ እግዚአብሔር ፈቃዱ ነው። ኢየሱስን እንደ አዳኝህ ስትቀበል ለኃጢአትህ ሁሉ ይቅርታን ታገኛለህ። እግዚአብሔርም ሰማያዊ አባትህ እንደሆነ ታውቃለህ። መንግሥተ ሰማይም ትገባ ዘንድ ዋስትና ታገኛለህ። መሢሑ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝህ ለመቀበል ውሳኔህ ከሆነ የሚከተለውን ጸሎት መጸለይ ትችላለህ። እግዚአብሔርም ይሰማሃል።

ኃያሉ እግዚአብሔር ሆይ፥ መሢሑ ኢየሱስ እንደሚወለድ፥ ለሥቃይና ለሞትም እንደሚዳረግና የሚጎናጸፈውን ታላቅ ክብር ሁሉ በመግለጽ ወደ ዓለም ከመምጣቱ ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምረው ነቢያት እንዲጽፉ ስላደረግህ አመሰግንሃለሁ። በመሢሑ ኢየሱስ በኩልም ለእኔ ያለህን ፍቅር ስለ ገለጽክልኝ በጣም አመሰግንሃለሁ። ለኃጢአቴ ስርየት መሢሑ ኢየሱስ ራሱን ለሞት አሳልፎ እንዲሰጥ ስላደረግክ አመሰግንሃለሁ። የዘለዓለምን ሕይወት እጎናጸፍ ዘንድ መሢሑ ኢየሱስን ከሞት ስላስነሣኸው አመሰግንሃለሁ። ኃጢአተኛ መሆኔን ጠንቅቄ አውቃለሁ። ኃጢአቴን ይቅር ትለኝ ዘንድም እለምንሃለሁ። ለእኔ ሲል ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ በሰጠው በመሢሑ ኢየሱስ ምክንያት ያገኘሁትን የኃጢአት ስርየት በዚችው ደቂቃ እቀበላለሁ። መሢሑ ኢየሱስ ጌታዬ ይሆን ዘንድ ፍላጎቴ ነው። ኢየሱስ ለሁሉ ያለውን ፍቅር ያህል እኔም ሌሎችን እወድ ዘንድ የዘለዓለም እርዳታህ አይለየኝ። ከኃጢአቴ ስላነጻኸኝ አመሰግንሃለሁ። ስለተቀበልከኝም አመሰግንሃለሁ። ይህን ሁሉ ጌታዬና አዳኜ በሆነው በመሢሑ ኢየሱስ ስም እለምንሃለሁ፤ አሜን።